# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከኦገስት 1-10/2022 የነበረው የአየር

## ሁኔታ ግምገማ እና

## ከኦገስት 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

## ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኦገስት 2022
አዲስ አበባ

ርዕስ ገፅ


እ.ኤ.አ ከኦገስት 1-10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ........3
ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10 /2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ........4
ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10 /2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት........5
ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10 /2022 ድረስ የነበረው የዝና ብመጠን........6
ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር........6
እ.ኤ.አ ከኦገስት 1-10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻ ሥራ........7
እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ........7
ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ........7
እ.ኤ.አ ከኦገስት 1-10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ........8
እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ........8
ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ........8
እ.ኤ.አ ከኦገስት 11-20/2022 የሚኖረው የአየር........9
ሁኔታ አዝማሚያ........9
ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 11-20, 2022_የሚኖረዉ ዝናብ በሚ.ሜ........10
እ.ኤ.አ ከኦገስት 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ........10
እ.ኤ.አ ከኦገስት 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ........11

## እ.ኤ.አ ከኦገስት 1-10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ


ባለፉት አስር ቀናት በየጣልቃዉ ፀሃያማ ሁኔታ የተስተዋለበት ሁኔታ የነበረ ቢሆንም፤ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ አካባቢዎች ወቅታዊዉን ዝናብ ማግኘታቸዉን ቀጥለዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ከነበረዉ ጠንካራ የደመና ክምችት በአንዳንድ የአማራ፣ በቤንሻንጉል-ጉሙዝ፣ በምዕራብና መካከለኛ ኦሮሚያ፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል እንዲሁም በደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ በ24 ሰዓታት ዉስጥ ተመዝግቧል፡፡ ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸዉ ጣቢያዎች መካከል አንዳንዶቹን ለመጥቀስ ያህል በባህርዳር 33.4፣ በሲሪንቃ 30.0ና 35.0፣ በደብረ ታቦር 32.8ና 38.3፣ በወረኢሉ 60.9፣ በኢጃጂ 32.2፣ በጊምቢ 31.2፣ በባሌ ሮቤ 39.4፣ በኢሊያይ 65.2ና 36.7፣ በአቦቦ 40.0ና 40.2፣ በላሬ 36.0፣ በአሶሳ 34.9 እና በወራቤ 34.1 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡

በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በትግራይ፣ በአማራ፣ በቤንሻንጉል-ጉሙዝ፣ በምዕራብና መካከለኛዉ ኦሮሚያ፣ በደቡብ ደጋማ ስፍራዎች፣ በሰሜን ሶማሌ፣ በሐረሪና ድሬዳዋ፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች፣ በሲዳማና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እንዲሁም አፋር ክልሎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ በብዙ ቦታዎች ላይ ተመዝግቧል፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በትግራይ፣ በአማራ፣ በቤንሻንጉል-ጉሙዝ፣ በአፋር፣ በጋምቤላ፣ በሲዳማ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እና በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልሎች ሁሉም ዞኖች፣ በሁሉም የወለጋና ሸዋ ዞኖች፣ በቡኖ በደሌ፣ በኢሉ አባቦራ፣ በጅማ፣ በአርሲና ምዕራብ አርሲ፣ በምዕራብ ሐረርጌ እና በሲቲ ዞኖች ላይ ከ25-172 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ4-10 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ በፋፈን፣ በምስራቅ ሐረርጌ፣ በባሌ፣ በጉጂና ምዕራብ ጉጂ ዞኖች አንዳንድ ቦታዎች ላይም ከ5-25 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ3 ላነሱ ቀናት ዝናብ ተመዝግቧል (ካርታ 1 እና 2)፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በትግራይ፣ ከምዕራብና መካከለኛዉ ጎንደር እንደሁም ባህረዳር ዙሪያ ጥቂት ቦታዎች በስተቀር በተቀሩት የአማራ ክልል ዞኖች፣ በአፋር፣ በቤንሻንጉል-ጉሙዝና ጋምቤላ ሁሉም ዞኖች፣ በቄለምና ምዕራብ ወለጋ፣ በሆሮ ጉዱሩና ምስራቅ ወለጋ፣ በጅማ፣ በቡኖ በደሌ፣ በምዕራብና ሰሜን ሸዋ(04)፣ በባሌ፣ በጉጂ፣ በምዕራብ ጉጂና በቦረና አብዛኛዉ ቦታዎች፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ በከፋና ምዕራብ ኦሞ፣ ከሞላ ጎደል በሁሉም የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝዝቦች ክልል እና ሲዳማ ክልል ዞኖች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ተመዝግቧል (ካርታ 3)፡፡


ካርታ 1    ኢ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10 /2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2 ኢ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10 /2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




## ካርታ 3   እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10 /2022 ድረስ የነበረው የዝና ብመጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



# እ.ኤ.አ ከኦገስት 1-10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የመጀመሪያዎቹ የኦገስት አስር ቀናት ለክረምት ዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተወሰነ ደረጃ አንጻራዊ ጥንካሬ የነበራቸው ሲሆን፤ ከዚህም ጋር ተያይዞ አብዛኛዎቹ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚና የመኸር ሰብል አብቃይ በሆኑት አካባቢዎች ላይ በመጠን ይለያይ እንጂ በስርጭት ረገድ ብዙ ቦታዎችን ያዳረሰ የእርጥበት ሁኔታ እንደነበራቸው ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተሰበሰቡ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህም የተገኘው እርጥበት ለመኸር የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ ላይ አዎንታዊ ሚና የነበረው ሲሆን፤ በተለይም አስቀድመው ለተዘሩም ሆነ በዘር ላይ ለሚገኙ የመካከለኛ ጊዜ የመኸር ሰብሎችም ሆነ በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀደም ብለው ለተዘሩ የረጅም ጊዜ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎችና ለተለያዩ የጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም በምስራቅ እና በሰሜን ምስራቅ ለሚገኙ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሳር ልምላሜ ጥሩ አስተዋጽኦ የነበረው ሲሆን፤ በተጨማሪም ሰው ሰራሽም ሆነ የተፈጥሮ ምንጮችን ከማጎልበት አንፃር አዎንታዊ ሚና ነበረው። በአንፃሩ በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የነበረው ከባድና ተከታታይነት የነበረው የዝናብ ሁኔታ ለወንዝ መሙላትና ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አንዳንድ አካባቢዎች ላይ የጎርፍ መከሰትም ሆነ የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛት እንዲኖር ከማድረጉ ጋር ተያይዞ በሰብል ሁለንተናዊ እድገት ላይ መጠነኛ አሉታዊ ተጽዕኖ ነበረው (ካርታ 4) ፡፡


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከኦገስት 1-10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ከኦገስት1-10/2022 የነበረው የእርጥበት ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በአብዛኛው የአገሪቱ ዋና ዋና የክረምት ተጠቃሚ ተፋሰሶችን ያዳረሰ እንዲሁም የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ የተስተዋለበት ነበር፡፡ ከነዚህም በአብዛኛው አባይ፣ አፋር ደናክል፣ ኦሞጊቤ፣ ባሮአኮቦ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ተከዜ፣ የላይኛው እና የታችኛው አዋሽ ኪስ ቦታዎች፣ በጥቂት የላይኛው ዋቢሸበሌ እና ገናሌዳዋና ተፋሰሶች ላይ ከከፍተኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ ተስተውሎባቸው ነበር፡፡ በሌላ በኩል በጥቂት የላይኛው ዋቢሸበሌ፣ ገናሌዳዋና በጥቂት የታችኛው ስምጥሸለቆና እንዲሁም የታችኛው አዋሽ አዋሳኝ ኪስ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ የእርጥበት ሁኔታ የተስተዋለባቸው ሲሆን፤ የተቀሩት ተፋሰሶች ደረቅና ከፊል ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ ስር ቆይተዋል (ካርታ 5)፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




# ኢ.ኤ.አ ከኦገስት 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ ከሞላ ጎደል ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከቀዳሚው አሥር ቀናት በበለጠ ሁኔታ እየተጠናከሩ የሚሄዱበት ጊዜ ነው፡፡ አልፎ አልፎ ባሉት ቀናትም ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ በረዶ የቀላቀለ ከባድ ዝናብ ለወንዞች ሙላትና ለቅጽበታዊ ጎርፍ መከሰት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት የተስፋፋና የተጠናከረ የወቅት ዝናብ በአብዛኛዎቹ የወቅቱ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ እንደሚኖርና የዝናቡ ስርጭትም ከቀዳሚዉ ቀናት አንፃር ወደ ሰሜን ምስራቅ ቆላማ አካባቢና ደቡብምዕራብ የሀገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች ላይ የተወሰነ መስፋፋት ሊኖረዉ እንደሚችል ይጠበቃል፡፡

በዚህ መሰረት በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በሰሜንምስራቅ፣ በሰሜንምዕራብ፣ በመካከለኛዉ እና በምእራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት ሊኖራቸዉ እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ሁሉም የወለጋ እና የሸዋ ዞኖች፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ቡኖ በደሌ፤ አዲስ አበባና አዲስ አበባ ዙርያ፤ የአማራ፣ የትግራይ፣ የአፋር፣ የጋምቤላ፣ የቤንሻንጉል-ጉሙዝ ክልል ዞኖች እና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሁሉም ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ሊያገኙ እንደሚችሉ ይጠበቃል። በተጨማሪም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከባድ ዝናብ ለቅጽበታዊ ጎርፍ መከሰት መንስኤ ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚህም ሌላ ምዕራብ ሐረርጌ፣ ሁሉም የአርሲ ዞኖች፣ ድሬዳዋና ሐረሪ፣ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ከደቡባዊ ዞኖች በስተቀር፤ የሲዳማ ዞኖች፤ ጥቂት የሰሜን ባሌ እና ጉጂ ዞኖች፣ እንዲሁም የሲቲ ዞኖች በአንዳንድ ሥፍራዎቻቸው ላይ በአብዛኛው ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው የሚጠበቅ ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች በአብዛኛው ከፍል ደመናማ ሆነው ይሰነብታሉ።




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 11-20, 2022
የሚኖረዉ ዝናብ በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከኦገስት 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በተሰጠው የአየር ሁኔታ ትንበያ መሰረት በሚቀጥለው የኦገሰት ሁለተኛዉ አስር ቀናት የመኸር ሰብል አምራች በሆኑትም ሆነ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች የሚኖረው እርጥበት ከቀደመው አሥር ቀናት አንጻር ሲታይ ከሞላ ጎደል የበለጠ ጥንካሬ ይዞ ሊቀጥል እንደሚችልና በተለይም ዝናቡ በሰሜን፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በመካከለኛዉ እና በደቡብ ከፍተኛ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ እርጥበት እንደሚኖራቸው ከመጠበቁ ጋር ተያይዞ በቀጣይ ለሚያከናውኑት የግብርና እንቅስቃሴ ገንቢ ሚና እንደሚኖረው ነው። በተጨመሪም የሚጠበቀው እርጥበታማ ሁኔታ በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች የዉሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም በአሁን ጊዜ እርጥበት በስፋት በማግኘት ላይ ላሉት በምስራቅና በሰሜን ምስራቅ ለሚገኙ አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽና የመጠጥ ዉሃ አቅርቦት ከማሻሻሉም በተጨማሪ የዝናብ ውሃን ለመሰብሰብና ለማጠራቀም ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በሌላ በኩል ከላይ በተጠቀሱት ከመደበኛ በላይ ዝናብ በሚጠበቅባቸዉ አንዳንድ ስፍራዎች በሚኖረው ከባድ ዝናብ ቅጽበታዊ ጎርፍ ከመፍጠሩ ጋር ተያይዞ በተለያየ የእድገት ደረጃዎች ላይ ላሉ ሰብሎች አሉታዊ ተፅዕኖ ስለሚኖረው ከባድ ዝናብ በሚጠበቅባቸው ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑና በውኃ መብዛት በሚጠቁ ቦታዎች አርሶ አደሩ እና የሚመለከታቸው አካላት በጋራ በመሆን የበዛውን ውሃ ከማሳ በማስወገድ የጎርፍ ውሃ መቀልበሻ ቦዮችን

በመስራት  ከወዲሁ ማዘጋጀትና በሰብሎች፣ በእንስሳትና በንብረት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል። እንዲሁም ከሰብል ጥበቃ አንፃርም ከእርጥበት መብዛት ጋር የአረም መከሰትና እንዲሁም በየጣልቃው ከሚኖረው ሙቀት ጋር ለፀረ ሰብል ተባይ መከሰት አመቺ ሁኔታን ሊፈጥር ስለሚችል አርሶ አደሩም ሆነ የግብርና ባለሙያዎች የማሳ ጉብኝት በየጊዜው በማድረግ አረምን በወቅቱ በማረምና ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በወቅቱ ከግብርና ባለሙያ በሚያገኙት ምክረ ሀሳብ በመደገፍ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከኦገስት 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የኦገስት ሁለተኛው አስር ቀናት በሰሜን፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በመካከለኛዉ እና በደቡብ ከፍተኛ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ እርጥበት መጠንና ሥርጭት ሊኖራቸዉ እንደሚችሉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በዚህም መሰረት በአብዛኛው አባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ ተከዜ፣ አዋሽ፣ አፋር ደናክል፣ አሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ በላይኛው ገናሌ ዳዋ እና ዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ከፍተኛ እርጥበት እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም በተጠቀሱ ተፋሰሶች ላይ በሚኖረው ተደጋጋሚ ከፍተኛ እርጥበት ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ በታዎች ላይ ለቅፅበታዊ ጎርፍ፣ ለወንዝ ሙላት እንዲሁም ለመሬት መንሸራተት ሊያጋልጥ ስለሚችል ከወዲሁ ክትትል ማድረጉ በንብረት እና በህይወት ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ ያስችላል፡፡ በተጨማሪም በታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣ በጥቂት የላይኛው ዋቤ ሸበሌ፣ በገናሌ ዳዋ ጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ መጠነኛ እርጥበት እንደሚኖራቸው የሚጠበቅ ሲሆን፣ የተቀሩት የደቡብ እና የደቡብ ምስራቅ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሆነው እንደሚቆዩ ይጠበቃል፡፡